# ሰው አይደለም የጠየቀን

የጠየቀን አርጉ ብሎ
የለመነን ስጡኝ ብሎ
የማይመልስ ብድር በቀን
በሃብታችን ጠላት ሆኖ የሚሸሽን
አቤ...ት ስስት ብሎ እሚለን
ተመልሶ ጠላት እንጂ ወዳጅ ዘመድ የማይሆነን፡፡
አይደል እሱ በሰውኛ
እየሞላ የሚያተርፈው ሁሌ ለእኛ፡፡
በጤና ላይ ጤና አድርጎ
በሃብትም ላይ ያማረውን ላቅ...አድርጎ፡፡
አትረፍርፎ ሞልቶ ሊሰጥ
በሰጠነው በትንሿ አድሮ በውስጥ፡፡
በበረከት ሊያስተውለን
እንዳንጠፋም ጥበቃውን ሊያበዛልን
ዙሪያ ገባው ሰላም ጤና እንዲሆነን፡፡
ብዝት...አድርጎ ፍቅር ደጋ
ለሰጠነው ለትን...ሿ ሰጥቶ ዋጋ፡፡
ከፍን እንጂ ዝቅን አያውቅ
ለሥጋ ነፍስ በጎ ደጉን የሚሰንቅ፡፡

> አትንኩብኝ የእኔን ድርሻ
> አትስረቁ የእኔን ድርሻ
> ፍዳሜውም ስለሚሆን መልካም ውጤት መጨረሻ፡፡
> ትዕዛዜን ተከተሉ ቃሌ ቃል ነው በመዝገቡ
> ሕጉ ሁሉ ለእናንተው ነው በበረከት መገደቡ፡፡

ሕጌን አውቆ ትዕዛዜን
ግድ የ቏ላ በረከቴን
ልጄ አብርሃም በተራራ ጭኖ ሂደ እንጨት ቢላ!
ሊሰዋልኝ አንድ ልጁን
የቃል ዕምነት በረከቱን፡፡
ዘር በዘር ላይ ሊበዛለት
ከከዋክብት ከአሸዋውም ሊልቅለት፡፡

> እያወቅነው እጁን ቀምሰን
> እያወቅነው እጁን አይተን
> እንዴት ኪሱን እንነካለን?

አቤል ብልህ ትዕዛዝ አውቆ
ለአመራረጥ ተጠንቅቆ
ከሰጠው ላይ የሰባውን
ጠቦት ሰዋ ያማረውን፡፡
ዓምላክ አየ የእሱን መርጦ
ሊባርከው ከቀረበው አበላልጦ፡፡

> ስጡኝና አርጉትና ፈትኑኝ
> ባላሞላው ባላተርፈው ታዘቡኝ፡፡

ሰው አይደለም የጠየቀን
ኤልሻዳይ ነው የፈጠረን
ከአሥር አንዱን ይቅር ብለን
መስጠት ማድረግ ለዓምላካችን
በትዕዛዙ ሳይከፋ በደስታ ውስጥ ልባችን፡፡

ስስት ለማን?
ለዓምላካችን ለፈጣሪ
መፈለጉ ምንዛሪ
በአምሳሉ ለፈጠረን
እየቻለ ደጋ ሰጥቶ ለሚያኖረን?

አይደል ብቻ ገንዘባችን፣
አይደል ብቻ ወርቅ ሀብታችን፣
ባናውቅ እንጂ ግልድ ባይሆን፣
ሁላችንም የእጁ ሥራ ሀብቱ እኮ ነን፡፡
ለማግኘቱ በረከቱን
አጥር ቅጥር እንዲሆነን
እንዳያረግፍ በእርሻ ወይኑን
እንዳንሆን የተረገምን
በትንሳዔው ግራ ቋሚ እንዳንሆን
በገባው ቃል ሊሸፍነን

ሰው አይደለም የጠየቀን
ኤልሻዳይ ነው የፈጠረን
ከአሥር አንዱን ይቅር ብለን
መስጠት ማድረግ ለዓምላካችን
በትዕዛዙ ሳይከፋ በደስታ ውስጥ ልባችን፡፡

ትንቢተ ሚልክያስ ምዕ 3:-7-18
በወ/ት አፎሚያ ሚካዔል ተዘጋጀ
የካቲት 2001 ዓ:ም